የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፳፭
አዲስ አበባ ግንቦት ፯ ቀን ፲፱፻፺፱

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

13th Year No 25.
ADDIS ABABA 15th May, 2007


ማውጫ


አዋጅ ቁጥር ፭፻፳፪/፲፱፻፺፱ ዓ.ም

ከኦፔክ ፈንድ ለዓለም አቀፍ ልማት ጋር የተደረገው የዕዳ ቅነሳ ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ … ገጽ ፫ሺ፮፻፩


CONTENTS


Proclamation No. 522/2007

OPEC Fund for International Development Debt Relief Agreement Ratification Proclamation Page 3601


## አዋጅ ቁጥር ፭፻፳፪/፲፱፻፺፱

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኦፔክ ፈንድ ለዓለም ዐቀፍ ልማት መካከል የተደረገውን የዕዳ ቅነሳ ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለዕዳ ክፍያ የሚውል ፮ ሚሊዮን ፭ መቶ ሺህ የአሜሪካን ዶላር /ስድስት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ የአሜሪካን ዶላር/ በብድር የሚያስገኘው የዕዳ ቅነሳ ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኦፔክ ፈንድ ለዓለም ዐቀፍ ልማት መካከል እ.ኤ.አ. ዲሴምበር ፳፩ ቀን ፪ሺ፭ በቪየና የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሚያዝያ ፲፮ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፤

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ /፩/ እና /፲፪/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ከኦፔክ ፈንድ ከዓለም አቀፍ ልማት ጋር የተደረገው የዕዳ ቅነሳ ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፭፻፳፪/፲፱፻፺፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## PROCLAMATION NO. 522/2007.

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE DEBT RELIEF AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE OPEC FUND FOR INTERNATIONAL DEVELOPMENT

**WHEREAS,** a Debt Relief Agreement**,** between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the OPEC Fund for International Development stipulating that the OPEC Fund for International Development provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan amount of six million Five hundred thousand United States Dollars (USD 6,500,000) to be used for debt servicing was signed in Vienna, on the 21st day of December 2005;

**WHEREAS,** the House of peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Agreement at its session held on the 24th day of April 2007;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 Sub-Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the " OPEC Fund for International Development Debt Relief Agreement Ratification Proclamation No.522/2007."

## ፪. <u>የስምምነቱ መፅደቅ</u>

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኦፔክ ፈንድ ለዓለም ዐቀፍ ልማት መካከል እ.ኤ.አ. ዲሴምበር ፳፩ ቀን ፪ሺ፭ በቪየና የተፈረመው በሂፒክ ኢንሼዬቲቨ ላይ የተመሠረተው የዕዳ ቅነሳ ስምምነት ፀድቋል።

## ፫. <u>የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ ሥልጣን</u>

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፮ ሚሊዮን ፭ መቶ ሺህ የአሜሪካን ዶላር /ስድስት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ የአሜሪካን ዶላር/ በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

## ፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወ ጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ግንቦት ፯ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**
**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ**
**ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 2. Ratification of the Agreement

The Enhanced HIPC Debt Relief Initiative Agreement signed between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the OPEC Fund for International Development on the 21st day of December 2005 is ratified.

## 3. Power of the Minister of Finance and Economic Development

The Minister of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan amount of six million five hundred thousand United States Dollars (USD 6,500,000) in accordance with the terms and conditions set forth in the Agreement.

## 4. Effective Date

This Proclamation shall come in to force up on Publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 15th day of May, 2007**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL**
**DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**